# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የጌታ እራት ፕሮግራም

ዛሬ የጌታ እራት ፕሮግራም ይኖረናል። ስለዚህ የከበረ ፕሮግራም ጌታ የተመሰገነ ይሁን።

### የአርብ ፕሮግራም

በአርቡ ፕሮግራማችን ጌታ እየባረከን ነው። በልዩ ልይ ጉዳዮች ላይ እንጸልያለን፤ ቃሉን እንማራለን። የምትችሉ እንድትካፈሉ እናበረታታለን። ጌታ ይባርካችሁ!

### የገንዘብ ማሰባሰቢያ ቅጽ

ለሕንጻ ግዢ የገንዘብ ማሰባሰቢያ የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልታችሁ ያልመለሳችሁ ወገኖች እባካችሁ ሞልታችሁ ለዲያቆናት ስጡልን። የህንጻ ኮሚቴ አስተባባሪዎች። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ:- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም:- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)

*"በሚመጣው ዘመን ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፥ እስራኤልም ያብባል ይጨበጭብማል፤ በፍሬያቸውም የዓለሙን ፊት ይሞላሉ።" (ኢሳ. 27፡6)*



⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
⇒ **Yeec.org App** ጭነዋል?
⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት:-
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| | | |
|---|---|---|
| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




## "... መንግስትህ ትምጣ ... "

(ማቴ. 6፡10)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**October 8, 2017**

**መስከረም 28፤ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ ፕሮግራም መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................ | እሕት ሰናይት ከበደ |
| አምልኮ...................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም  አያሌው አስፋው |
| ቃል ........................... | ወንድም ብርሃኑ አንበሴ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

“ወይስ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ እቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል? ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል።”
(ማቴ. 12፡ 29)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 6602 N. Damen Ave., Chicago IL 60626 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ  ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወቤን | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ጸሎት አስተምረን -- መንግስትህ ትምጣ (ክፍል አምስት)

*“እርሱም በአንድ ስፍራ ይጸልይ ነበር፥ በጨረሰም ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፦ ጌታ ሆይ፥ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ እንጸልይ ዘንድ አስተምረን አለው። አላቸውም፦ ስትጸልዩ እንዲህ በሉ፦ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ... <u>መንግስትህ ትምጣ</u> ...” (ሉቃ. 11፡1-2)*

ባለፈው ሳምንት እንዳየነው ጌታ ባስተማረን ጸሎት ውስጥ የምንጸልየው አንዱ ጸሎት “መንግስትህ ትምጣ” ብለን ነው። ዛሬ ስለዚህ ጸሎት ተጨማሪ ሃሳቦችን እናያለን።

መንግስትህ ትምጣ ብለን ስንጸልይ የእግዚአብሔር ኃይልና ሕልውና በሕይወታችን፣ በቤተ ክርስቲያን እና በምንኖርበት አካባቢ እንዲገዛ መፍቀዳችን ነው። የመንግስታት ግንኙነት የኃይል ግንኙነት ነው። አንድ መንግስት ተጽንኦ በሚያሳድርበት ስፍራና ሁኔታ ሌላ መንግስት ተጽንኦ ማሳረፍ አይችልም። የእግዚአብሔር መንግስት በኃይል በምትሰራበት ስፍራ የጨለማው መንግስት መስራት አይችልም። የግዚአብሔር መንግስት የብርሃንና የጽድቅ መንግስት ስልሆነ የጨለማ ኃይል በፊቱ ሊቆም አይችልም። ስለዚህ የጌታ መንፈስ ባለበት ስፍራ ሁሉ አርነት አለ። ስለዚህ ነው የእግዚአብሔር መንግስት በምትገዛበት ስፍራ ሁሉ ሰዎች ከተለያየ እስራት የሚፈቱት። መንፈስ ቅዱስ በሚሰራበት ስፍራ የሚገለጠው የእግዚአብሔር መንግስት ነው። ጌታችን “እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች” ብሎናል። (ማቴ. 12፡28) አጋንንት ሰዎችን ለቀው የሚወጡት ከእነርሱ በሚበልጥ ኃይል ብቻ ነው። ያም ደግም የእግዚአብሔር መንግስት ኃይል ነው። ቤተ ክርስቲያን በምድር የእግዚአብሔር መንግስት መገለጫ ስለሆነች የገሃነብ ደጆች አይችሏትም። ያቆማትና የሚደግፉት ብርቱ የሆነው የእግዚአብሔር መንግስት ኃይል ነው።

ሌላው ስለ እግዚአብሔር መንግስት ጉዳይ መረዳት ያለብን ነገር የእግዚአብሔር መንግስት ከምንም በላይ የምንፈልጋት መሆን እንዳለበት ነው። ለዚህ ነው ቃሉ “መንግስትህ ትምጣ” ብላችሁ ጸልዩ የሚለን። ስለዚህም አስቀድመን የእግዚአብሔርን መንግስትና ጽድቅ መፈለግ አለብን። ጌታ በብዙ ምሳሌ እንዳስተማረው የእግዚአብሔር መንግስት ያለንን ሁሉ ሸጠን እንደምንገዛት የከበረ መዝገብ ነች። የእግዚአብሔር መንግስት ያለንን ሁሉ ሸጠን እንደምንገዛት የከበረ እንቁ ነች። የሚተካከላት የለም። በክርስቶስ ያገኘነውን በመንግስቱ ውስጥ የመግባት ሕይወት በምንም ልንለውጠው ወይንም ከምንም ጋር ልናነጻጽረው አንችልም። ሐዋሪያው ጳውሎስ በምድር ሊመካበት ከሚችለው ነገር ሁሉ በላይ በክርስቶስ ያገኘው ሕይወት እንደሚልጥ መስክሯል። እንዲያው ስለ ክርስቶስ ሌላውን ሁሉ እንደ ጉድፍ (ፋንድያ) እንደሚቆጥረው ተናግሯል። ለኛም እንዲሁ ነው። የተቀበልነው ሕይወት፣ በወንጌል አምነን የግዚአብሔር ልጆችና የመንግስቱ ዜጎች መሆናችን የከበረ ነው። እግዚአብሔር ሆይ “መንግስትህ ትምጣ።” (ይቀጥላል)